<u>ሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞ እንጂ መለመማጥ አይደለም</u>

ይቅር ደምዜ

አይታክቴ ታጋይ ወንድሙ መኮንን ከለንደን ከላከው የሰሞኑ መልዕክት ድህረ ገፅ ላይ ሳይ ሀገር ወዳድ ሰልፈኞች የያዙት መፈክር "ፕሬዚዳንት ቡሽ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ነህ ወይስ ከአምባገነኑ ጋር" የሚል ጥያቄን የያዘ ነበር። ሰልፈኞቹ በለንደን ከተማ በአሜሪካን ኤምባሲ ላይ ሰልፍ አካሂደዋል። ግሩም ድንቅ በርቱ ወገኖቼ።

ለመፃፍ ያነሳሳኝ ጉዳይ ግን የምናደርገውን ሰልፎች የሚመለከት ነው። በምኖርበት በዋሺንግተን ከተማ ብዙ ስልፎች ላይ ተካፍያለሁ። አንዴ ተንበርክክን እንፀልይ ብሎ በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊት ለፊትም አንበርክኮ ያዋረደን ነበር። በየሰልፉ ግን "ኮንዶሊዛ ራይስ ረሳሽን ወይ?"፤ "ፕሬዚዳንት ቡሽ ረሳኸን ወይ?" በሚል ዓይነት ልመናና ምለላን ያስቀደሙ ሰልፎች ነበሩ። በዱሮ ሰልፎች ማለትም በአዲስ አበባ የአሜሪካ ባንዲራ ሲቃጠል እንጂ በክብር ሲያዝ አልታየም--ግን ትላንት ዛሬ አይደለም ምን ያስገርመናል እንዳለው ነው ዘፋኙ። ሰልፎች የቁጣ መሆናቸው ቀርቶ የልምምጥ ሆነው ይታያሉ። በጣም ጭምትና አሜሪካና እንግሊዘን የሚቃወሙ ሳይሆኑ የሚለምኑ ዓይነት ናቸው። አሜሪካ ኢሕአዴግን በመደገፉ በመወገዝ ፈንታ አቤት እርዳን በሚል ምለላ የሚገባው አልነበረም/ አይደለም። ወደ ቀድሞ የተቃውሞ ክንውኖች መለስ ካልን ደግሞ ተራማጆች ኤምባሲዎችን እየያዙ ሳይቀር ጠላትን ጠላት ብለው የታገሉበት፤ ሰልፎች በመዝሙርና ደማቅ ተቃውሞ ከተሞችን ያናወጡበት ሁኔታ ነበር። ጆርጅ ቡሽ የአሜሪካ መሪ ነው። ኮንዶሊዛ ራይስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ናት። እነዚህ ሰዎች፤አስተዳደራቸው ከመለስ ጎን በግልፅ ቆመዋል። ከእነዚህ የሚጠበቅ ስርየት ሊኖር አይችልም። ታዲያ ለምን ይበጃል ልምምጡ? ዳውን ዊዝ ዩ ቡሽ፤ ዳውን ዊዝ ዩ ብሌይር፤ ወይንም ክዋሜ ንክሩማህ ይል እንደነበረው ኢትዮጵያ ሻል ትራያምፍ/ ኢትዮጵያ በጠላቶቿ ላይ ድልን ትቀዳጃለች ማለቱ አይሻልም?

ጎበዝ-- ጠላትና ወዳጅን መለየት ካቃተንማ ትግሉን መተዋችን ይመረጣል። አሜሪካ ወዳጅ አይደለም። ስልት ከተባለ ደግሞ አድነኑ-- ኪራርይሶን ለቡሽና ራይስ ማሰማቱ ቅሌት ነው። ካለመስማታቸው ሌላ ምንም አልገባቸውም ብለው ይታዘቡናል። አይደነግጡም ይስቁብናል። ሲለምኑ ደግሞ ይጀነናሉ እንጂ አያዝኑልንም። በመሰረቱ የተቃውሞ እርምጃ ከተባለ ፈርጠም ብሎ መከሰት ያለበት እንጂ መልፈስፈስን የሚጠይቅ አይደለም። ታዲያ ሰልፍ ሰናደርግ ብሌይር አድነን፤ ቡሽ ታደገን፤ ራይስ ነፍሳችንን አውጪን ብሎ መጮሁ ያስገምተናል፤ ያዋርደናል። ከጠላታችን ጋር የወገኑትን አድኑን ማለቱ ቅሌትና-- ይቅርታ አድርጉልኝና-- ከሞኝነትም አልፎ ድንቁርና ነውና ነው። ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ሰባ ዓመት ደነቆሩ እንዳይሆን ካለፈውም መማር ያስፈልጋል። እኔ የተካፈልኩባቸው ሰልፎች ጨዋ ከመሆናቸው የተነሳ አስከሬን የምናጅብ መስለን ነበር። አትለውም ወይ የለ ሌላ፤ አርድ አንቀጥቅጥ መፈክር ወይ መዝሙር የለ--ሚስተር ቡሽ ሴብ ኣስ ብቻ፤፤ አድነን ቡሽ፤አሳዛኝ፤ አሳፋሪ። የዛሬ ፖለቲከኞች ካለፈው ላለመማር የማሉ የተገዘቱ ይመስላሉ። ለምን? መልሱ ለእኔ ግልፅ አይደለም። አለማወቁ ከዘመዴ መራቄ ሊሆን ይችላል። ግን አለማወቅን ማወቅ ደግሞ ፀጋ ነው። ፀረ ወያኔ ሰልፎች የጠላት ዘመድና የቤንዚን ዓመድ የለውም ማለት አለባቸው። አሜሪካና እንግሊዝን መማጠን መለመን ሳይሆን ማውገዝ፤ ሰልፎቹን ማጮህ ያሻል ማለት ነው።

ስለዚህም በተቃውሞ ሰልፎች ማሳየት ያለብን ስሜትና ምሬት እንጂ የቀዘቀዘ የልመናና መማፀን ሁኔታ መሆን የለበትም፤ የሰልፍ መፈክሮቻችን በጥንቃቄ ይዘጋጁ። ከልመና ቃና ይለያዩ። ቁጣና ምሬታችንን ያስተጋቡ። ይጩኹ። ይበጥብጡ። ያኔ አድማጭ እናገኛለን። አትለውም ወይ እንበል። እንዘምር። ለተነሳ ሕዝብ ተነስ ተነስ ማለቱንም እንተው። ዘራፍ ይደመጥ። ኢትዮጵያ ስርየቷን ከማንም ባዕድ እንደማትጠብቅ እንንገራቸው። አንቅለስለስ። ቡሽም ሆነ ብሌይር ከእኛ ጋር አለመሆናቸውን አውቀን እንጩህባቸው። በአጭሩ እስቲ የምንሰለፈው፤ የምንጮኸው ተቃውመናቸው መሆኑን እናሳያቸው። ባንዲራቸውንም አጋይተን ተመልከቱን እንበላቸው። ስንሰለፍም የእነሱን ባንዲራ ማንገቡን ማውለበለቡን እስቲ እናቁም። የወያኔን ወዳጅ ባንዲራ ማውለበለቡና ተቃዋሚ ነን ማለቱ አብሮ አይሄድም። የኢተዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ብቻ እንያዝ። ማንንም አንለምን። ይህ ምን ያቅታል ጎበዝ?

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com